# ሙታን ድምፁን ይሰማሉ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሁለተኛ መምጣት በአንድ ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜያት በከፍተኛ ስሜት ለምእመናን ታስተምራለች የምታስተምርባቸውም ዕለታት አንደኛው በጌታችን በመድኃኒታችን ጾም እኩሌታ በሚውለው ደብረ ዘይት ተብሎ በሚጠራው ዕለተ ሰንበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚገኘው ወርኃ ጳጉሜን ነው ።

በተጠቀሱት ወራት ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚመጣ ታስተምራለች አንዳንድ አበው ሊቃውንት ደግሞ የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት መታወስ ያለበት በአንድ ዓመት ውስጥ አራት ጊዜያት ነው፣ይሉና ለዚሁ ማስረጃ ሲያቀርቡ ቅዱስ ድሜጥሮስ ቀመረሐሳብ በፊት አንዱን አመት 4ቱ ወንጌላውያን 91 ቀን 91 ቀን እየተካፈሉ ይመግቡት ነበር የእያንዳንዱ ወንጌላዊ ድርሻም በተፈጸመ ጊዜ የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ይታወስ ነበር ይኸውም አሁን እኛ በዓመቱ መጨረሻ በጳጉሜ እንደምናስታውሰው ማለት ነው ይሉና ቅዱስ ያሬድም ቢሆን ስለ ክርስቶስ መምጣት የዘመረው በሁለት ወራት ብቻ አይደለም በማለት ይናገራሉ ።

ያም ሆነ ይህ የክርስቶስን ሁለተኛ መምጣት የሰው ልጆች ሁሉ እንዳይዘነጉት እንዲያስታውሱት አስተውለውም ለመልካም ሥራ እንዲዘጋጁ እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም መቼም ቢሆን ክርስቶስ ሁለት ጊዜያት ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ቀደም ብሎ ተነግሯል አንደኛው ማለት በሥጋ የሚመጣበት አመጣጥ ተፈጽሞ ሁለተኛው በባሕርይ ክብሩ ዋጋ ለመክፈል የሚመጣበትን ፡ ሁላችን በተስፋ እንጠባበቃለን ።

የክርስቶስ የመጀመሪያ አመጣጡ ስለ ሰው ልጆች በደልና ኃጢአት ለመሞትና ሞቶም የሰውን ልጆች ከፍዳና ከመርገም ነፃ ለማድረግ ነበር እንግዲህ ወዲህ ግን ክርስቶስ ሁለተኛ ስለሰው ልጆች በደልና ኃጢአት ለመሰቀልና ለመሞት አይመጣም ሁለተኛ የሚመጣው መልካም ለሠሩ ሰዎች ዋጋቸውን መንግሥተ ሰማያትን ፤ ክፉ ሥራ ለሠሩ ደግሞ ፍዳቸውን ለመስጠት ነው ።

ክቡር ዳዊት ይህንን በመዝሙር ሲገልጽ“ እግዚአብሔር ግልጽ ሆኖ ይመጣል አምላካችንም ዝም አይልም፤እሳት በፊቱ ይንቀለቀላል በዙሪያውም ብዙ አውሎ አለ በላይ ያለውን ሳማይን ምድርንም በሕዝቡ ለመፍረድ ይጠራል” ብሏል መዝ 49 . 3 ።

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ፍርድ መስጠት በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ስለሆነ የሚያጠራጥር ባይሆንም የሚመጣበት ወርኅ ዘመን፤ዕለት ሰዓት ተለይቶ ሊታወቅ ከቶ አይችልም ። ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት በጣም ቀራቢዎች እንደመሆናቸው መጠን አንድ ጊዜ ደብረ ዘይት በሚባለው ቦታ ብዙ ሕዝብን ሰብስቦ ስለ ሁለተኛ አመጣጡ ሲያስተምር ለብቻቸው ሆነው የሚመጣበት ወርኅ ዕለቱንና ሰዓቱን እንዲነግራቸው ጠይቀውት ነበር ክርስቶስ ግን የሚመጣበትን ወርኅ ዕለትና ሰዓት ወስኖና ቆርጦ አልነገራቸውም ።

ይሁን እንጂ የሚመጣበት ወራት በተቃረበ ጊዜ ከሚፈጸሙት ምልክቶች አልፎ አልፎ ነግሯቸዋል ፡ ክርስቶስ ለሐዋርያት ከነገራቸውም የምጽአት ምልክቶች ጥቂቶቹን እንመለከታቸዋለን ፤ “ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙዘንድ ግድ አላችሁ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና ረኃብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል ከአመጽ ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች እስከ መጨረሻው የሚታገሥ ግን ይድናል” ካለ በኋላ “ስለዚያች ቀንና ሰዓት የሚያውቅ የለም” በማለት የደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ ዘግቶታል ማቴ 24. 5 ፤ 12 - 26

ስለክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት የተነገሩት ምልክቶች ሲፈጸሙ ባየንና በሰማን ጊዜ ልናደርጋቸው የሚገቡትን ጥንቃቄዎች ራሱ ክርስቶስ ነግሮናል “ያን ግን እወቁ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍለ ሌሊት ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ በነቃ ቤቱንም ሊቆፍር ባልተወም ነበር ፤ ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ በማታስቡት ሰዓት ይመጣልና ብሏል ማቴ 24.44

ለክርስቶስ ሁለትኛ መምጣት የሚያስፈልገው ዝግጅት በእግዚአብሔር ያለውን እምነት አጠንክሮ ፤ስነ ምግባርን አሳምሮ በሚገባ ተዘጋጅቶ መቀመጥ ነው ሰዎች ምጽዓቱን ዘንግተው ሃይማኖታቸውን አላልተው ምግባር ትሩፋታቸውን ርግፍ አድርገው ትተው በንዝህላልነት እንዳይኖሩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በየጊዜው መልእክቷን ከማስተላለፍ አትቦዝንም ።

ክርስቶስ ሁለተኛ በመጣ ጊዜ ስለሚፈጸመው ድርጊት በማቴዎስ ወንጌል እንደሚከተለው ተጽፏል “የሰው ልጅ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ መላእክትን አስከትሎ በባሕርይ ክብሩ በመጣ ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል ፡ አሕዛብም በፊቱ ይሰበሰባሉ ንጉሥ ክርስቶስም ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ ያቆማቸዋል” ይልና ፡

በመጀመሪያ ጻድቃንን እናንተ የአባቴ ወዳጆች ኑ ዓለም ሳይፈጠር ዘመን ሳይቆጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ሰማያት ውረሱ በማለት በምድር በሠሩት መልካም ሥራ የማታልፈውን መንግሥተ ሰማያት ያወርሳቸዋል፤እን

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ዲሁም ኃጥአንን እናንተ ርጉማን ለሰይ ጣንና ለመሰሎቹ ወደተዘጋጀላቸው ገሃ ነመ እሳት ሂዱ በማለት የመጨረሻ ፍርዱን ያስተላልፋል ፤ ከዚያ በኋላ ጻድ ቃን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ኃጥአን ግን ወደዘለዓለም ፍዳ ይሄዳሉ ማቴ 25. 31-46 ፤

ይህንንም በዮሐንስ ወንጌል ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ ሲናገር "በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ፡ ክፉም ያደበረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይነ ሣሉ" ብሏል ዮሐ 5. 25 - 29

ሙታን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰም ተው መቃብር ክፈቱልን መግነዝ ፍቱ ልን እቀፉን ደግፉን ሳይሉ ተነሥተው የመጨረሻው ዋጋቸውን የሚያገኙበት ዕለት በክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ስለሆነ በዚያ ቀን ዓለም ሳይፈጠርዘመ ን ሳይቆጠር ወደ ተዘጋጀችው መንግ ሥተ እግዚአብሔር ገብተን በማይለ ወጥ ዘለዓለማዊ ደስታ ለመኖር እንድን በቃ እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ አጠንክረን ሥነምግባራችንን አሳምረን እንጠብቀው ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ

ትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 47 ነሐሴ 1973

www.ethiopianorthodox.org